OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የሲቪክ ገጣሚ 2025-26 መመሪያዎች

## የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ

የሲያትል የስነ ጥበባት እና የባህል ጽ/ቤት (ARTS) ከሲያትል ከተማ የስነጽሁፍ ስራዎች ጋር በመተባበር አንድ ልምድ ላለው ገጣሚ የሁለት አመት የነዋሪነት የሥራ ማስፈጸሚያ ክፍያ እና ድጋፍ ይሰጣል። የሲቪክ ገጣሚው ለሲያትል ብልጽግና፣ ባለ ብዙ ቀለም የስነ-ጽሁፍ መልክዓ ምድር እና የሲያትል የተለያዩ የባህል ማህበረሰብን የሚወክል የባህል አምባሳደር ነው። የተመረጠው ተሸላሚ ከ2025 መጀመሪያ እስከ 2026 መጨረሻ ድረስ ያለውን ሁለት ዓመታት ኮሚሽናቸውን $25,000 ዶላር ይቀበላል። ከዓመታዊ የከተማ ዝግጅቶች በተጨማሪ የሲቪክ ገጣሚው የስነ-ጽሑፍ ጥበብን እያከበረ ባለበት ጊዜ በከተማው፣ በህዝቡ እና በሌሎች አርቲስቶች መካከል የማህበረሰብ ውይይት እና ተሳትፎን ያሳድጋል።

እንደ የከተማዋ የሁለት ዓመት የግጥም አምባሳደር፣ የሲቪክ ገጣሚው ሚና አመታዊ የስራ እቅድ ማውጣት/ ማዳበር፣ ከተማ አቀፍ ሰፋ ያሉ የፈጠራ እድሎችን ማከናወን እና በየአመቱ መጨረሻ ላይ የመዝጊያ መግለጫ መስጠት ነው። እነዚህ እድሎች ንባብን፣ አውደ ጥናቶችን፣ ፕሮጀክቶችን፣ እና እንዲሁም የንግግር ተሳትፎዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ – ሁሉም ከሥነ ጽሑፍ እና ከማህበረሰብ ጥንድ ህብር ጋር በማስኬድ። የሲቪክ ገጣሚው የግጥም ዋጋን በማስተዋወቅ ከፍ እያስደረገ ማህበረሰቦችን፣ የከተማ መምሪያዎችን እና ነዋሪዎችን የሚያገናኙ እና የሚያሳትፉ ህዝባዊ ክስተቶችን ያዘጋጃል። እንደ አንድ የተመደበ አቅራቢ፣ የሲቪክ ገጣሚው በሁለት አመታዊ ህዝባዊ ዝግጅቶች ከሲያትል ከተማ የስነ-ጽሁፍ እና ከብሔራዊ የግጥም ወር ጋር ይሳተፋል።

**ለማመልከቻው፣ ለብቁነት ወይም ለመስመር ላይ የቴክኒክ ድጋፍ መረጃ እና እርዳታ ለማግኘት፣** የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅን ዛክ ፍሪመል (Zach Frimmel)ን በ **(206) 963-9226** ወይም ኢሜይል Zach.Frimmel@seattle.gov ያግኙ።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪዲዮ በኩል) ጨምሮ በእርስዎ ቋንቋ እርስዎን ሊያነጋግሩ የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** ብቻ ይደውሉልን እና እርስዎ የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። አስተርጓሚ ስናፈላልግ ጥሪውን እስከሚቀላቀለን ለአጭር ጊዜ እንደሚያስጠብቅዎት ከወዲሁ ይወቁ።

## ማመልከቻ

በመስመር ላይ በ Submittable በኩል ያመልክቱ። ለማመልከት ነፃ ነው:-

ኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ከሌለዎት፣ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ፣ ዛክ ፍሪመል (Zach Frimmel)ን በ **(206) 963-9226** ወይም Zach.Frimmel@seattle.gov ያግኙ።

## የማብቂያ ዕለተ ቀን

ማክሰኞ፣ ነሐሴ 20 ቀን 2024፣ ከምሽቱ 5 ሰዓት (ፓስፊክ)

## ብቁነት

ይህ ጥሪ የታተሙ/በራስ የታተሙ ስራዎች፣ በቃል የተነበቡ/በንግግር የተያዙ፣ የፕሮጀክት እቅድ ልምድ እና የተተገበረ የዘር ፍትሃዊ እኩልነትን ጨምሮ የተመሰረተ የስራ አካል ላላቸው ሲያትልን መሠረት ላደረጉ ገጣሚዎች ክፍት ነው። የሚከተሉትን ካሟሉ ብቁ ይሆናሉ:-

- የመኖሪያዎ መሠረት ሲያትል ከሆነ (መኖሪያዎ በሲያትል ከተማ ውስጥ ነው)
- በአሜሪካ ውስጥ ለመስራት ብቁ ከሆኑ
- በማመልከቻው የማብቂያ ዕለተ ቀን የእርስዎ እድሜ 18+ አመት ከሆኑ
- በማመልከቻው የማብቂያ ዕለተ ቀን በማንኛውም ደረጃ ተማሪ ሆነው ያልተመዘገቡ ከሆኑ
- በኪነ ጥበብ በኩል ፍትሃዊ እኩልነትን እና ማካተትን በማስተዋወቅ ፍላጎት/ልምድ ያሳዩ ከሆኑ
- ከሽርክናዎች ጋር ጠንካራ የፕሮግራም እቅድ ማውጣት እና ትግበራን ያሳዩ ከሆኑ

## የድጋፍ ገንዘብ

የሁለት አመት የሲቪክ ገጣሚ የሥራ ማስፈጸሚያ ክፍያ **$25,000 ዶላር ነው።** የገንዘብ ድጋፍ ለሁለት ዓመት ጊዜ ነው እና ለጽሑፍ፣ ለአስተዳደር፣ ለአርቲስት ክፍያዎች፣ ለአፈፃፀሞች፣ ለዝግጅት ወጪዎች፣ ለቁሳቁሶች፣ ለጉዞዎች፣ ለክፍያዎች፣ ለግብሮች እና ለሌሎች ከፕሮጀክት ጋር ለተዛመዱ ወጪዎች መሸፈኛ ነው።

## የመረጃ ክፍለ ጊዜ (ድብልቅ)

ስለ ፕሮግራሙ በበለጠ ይወቁ እና ከሁሉ ምርጥ የሆነ የእርስዎን ማመልከቻ እንዴት ማስገባት እንደሚችሉ ይረዱ።

ሰኞ፣ ሐምሌ 22 ቀን፣ ከሰዓት ከ1 - 3 (ፓስፊክ)
**በአካል**:- ARTS at King Street Station
303 S Jackson St, Seattle, WA 98104 (ላይኛው ፎቅ፣ ክፍል 315)
**ምናባዊ**:- Microsoft Teams
**[እባክዎን መልስ ይስጡ]**

### የማመልከቻ ረቂቅ መከለሻ/ ግምገማ የማብቂያ ዕለተ ቀን

ማክሰኞ፣ ነሐሴ 6፣ ከምሽቱ 5 ሰዓት (ፓስፊክ)

አመልካቾች እስከ ነሀሴ 6 ከምሽቱ 5 ሰአት (ፓሲፊክ) ድረስ ለግምገማ እና ለግብረ መልስ የረቂቅ ወረቀት/ጽሑፍ ማቅረብ ይችላሉ። **ከሐምሌ 6 በኋላ**፣ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች ሙሉ ግብረ መልስ መስጠት አይችሉም ነገር ግን ማንኛውንም ጥያቄዎች ለመመለስ እና ብቁነት ወይም ማመልከቻ መሟላቱን ለማረጋገጥ እዚያ ይገኛሉ።

### የማመልከቻ እርዳታ

የማመልከቻ እገዛን ለመጠየቅ፣ የስልክ ወይም የምናባዊ ስብሰባ ቀጠሮ ለመያዝ እስከ ነሀሴ 6 ድረስ ለፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ዛክ ፍሪመል (Zach Frimmel)ን በ Zach.Frimmel@seattle.gov ኢሜይል ይላኩ።